**«…ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ወደ እኔ ተመለሱ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ ይላል ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር። »**

***(ት. ዘካ ፩፥፫)***

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች

፬ መልእክት

፮ ሪፖርታዥ

፱ ቤተ አብርሃም

፲፪ ቃለ መጠይቅ

፲፭ የሕፃናት ዓምድ

፲፯ ትዝብት

፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ





## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ

ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ

ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# ማኅበረ ቅዱሳን የአብነት ትምህርት ቤቶችን የማስፋፋትና የማጠናከር ሥራዎችን እየሠራ እንደሆነ ገለጠ

*በኃይሁን ለምለሙ*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን የአብነት ትምህርት ቤቶችን የማስፋትና የማጠናከር ሥራዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ እንደሆነ የቅዱሳት መካናትና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት ማስተባበሪያ ምክትል ኃላፊ ዲ/ን አንድነት ተፈራ ገለጡ።

በአብነት ትምህርት ቤቶች ማስፋፊያ መርሐ ግብር ላይ የአብነት ትምህርት ቤቶች የሌላቸው አካባቢዎች ተለይተው አዳዲስ ትምህርት ቤቶች የሚቋቋሙ ሲሆን በማጠናከሪያ መርሐ ግብር ደግሞ የአብነት ትምህርት ቤቶችን የማሻሻልና የመደገፍ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ም/ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን ሃያ አምስት አህጉረ ስብከት ለይቶ የአብነት ትምህርት ቤቶችን በትኩረት እየሠራ እንደሚገኝ የገለጡት ኃላፊው "በዚህ ዓመት ብቻ በአራት አህጉረ ስብከት የአብነት ት/ቤቶችን ለመሥራት እቅድ ይዟል" ብለዋል፡፡ እቅድ ከተያዘላቸው አራት አህጉረ ስብከት መካከል አፋር፣ ሶማሌ፣ አርሲና ምሥራቅ ወለጋ አህጉረ ስብከት እንደሚገኙበት ያስታወቁት ኃላፊው የሶማሌ ሀገረ ስብከት የአብነት ትምህርት ቤት በቅርቡ የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠለት ሲሆን በቅርቡም የግንባታ ሥራው እንደሚጀመር ተናግረዋል፡፡ ሌሎች ተመሳሳይ የአብነት ትምህርት ቤቶች ግንባታም በሂደት ሥራቸው እንደሚጀመር አስረድተዋል፡፡

አዲስ በሚቋቋሙ የአብነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአካባቢያቸውን ባህልና ቋንቋ ጠንቅቀው የሚያውቁ ወጣቶች ተመልምለው እንደሚገቡ ያስረዱት ኃላፊው በሚኖራቸው የሁለት ዓመት ቆይታም የቤተ መቅደስና የዐውደ ምህረት አገልግሎትን እንደሚቀስሙ ተናግረዋል፡፡

ኃላፊው አያይዘውም ማኅበረ ቅዱሳን የአብነት ት/ቤቶችን ከማቋቋምና ከማጠናከር ባሻገር ጊዜያዊ የገንዘብ ድጋፍም እንደሚደረግላቸው ተናግረዋል፡፡ አጠቃላይ ለተማሪዎችና ለመምህራን የሚደረገው ወርኀዊ የገንዘብ ድጋፍ በዓመት እስከ አምስት ሚሊዮን እንደሚደረስም አስረድተዋል፡፡



ዲ/ን አንድነት ብርሃኑ
(የቅዱሳት መካናትና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት ማስተባበሪያ ምክትል ኃላፊ)

ባልታወቀ ምክንያት ጥር ፺ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም የሳት ቃጠሎ አደጋ የደረሰበት በምእራብ ጎጃም ሀገር ስብከት የጨጎዴ ሃና የቅኔ ማስመሥከሪያ ጉባኤ ቤት በአዲስ መልክ እየተሠራ መሆኑን ም/ኃላፊው ተናግረዋል፡፡ የቅኔ ማስመስከሪያ ጉባኤ ቤት ፕሮጀክት የተጀመረው ፳፻፪ ዓ.ም ሲሆን ለፕሮጀክቱ የዋለውን ፲ ሺህ ካሬ መሬት የሰጠው የምእራብ ጎጃም ዞን የቋሪት ወረዳት መንግሥት ነው፡፡

ፕሮጀክቱ የተማሪዎች ማደሪያ፣ የመምህራን መኖሪያ፣ የተማሪዎች መፀዳጃ ቤትና የምግብ ማብሰያ ያካተተ ሲሆን ሲጠናቀቅም በርካታ ነባርና አዳዲስ ተማሪዎችን ተቀብሎ እንደሚያስተናግድ ም/ኃላፊው ገልጸዋል፡፡ ፕሮጀክቱ ከ፵፳ በመቶ በላይ የደረሰ ቢሆንም በዚህ ወቅት ግን የበጀት እጥረት እንደገጠመው አስረድተው የተፈለገው ያህል በጀት የሚገኝ ከሆነ ግን በቅርቡ መጠናቀቅ እንደሚችል አስታውቀዋል፡፡

የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጭ እስከ አምስት ሚሊዮን ብር የሚደርስ ሲሆን ከዚህ ቀደም ወጭ የተደረገው ገንዘብ ከምእመናን ድጋፍ የተገኘ መሆኑን ያነሱት ኃላፊው "አዳዲስ የሚቋቋሙና ነባር የአብነት ትምህርት ቤቶች ራሳቸውን በገቢ የሚችሉበትን መንገድ መፈለግ ያስፈልጋል" ሲሉም ተናግረዋል፡፡

# “የአንገት ማዕተቤን አላወልቅም” ያለው ወጣት ከሥራ ገበታው ተሰናበተ


በካሣሁን ለምለሙ

ፊሪነቱን ስዊድን ያደረገው የሃያ ስምንት ዓመቱ ጆርጅ ታኑዋሪ ‹‹የአንገት ማዕተቤን አላወልቅም›› በማለቱ ከሥራ ገበታው ተሰናበተ። የሶሪያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ የሆነው ጆርጅ ተቀጥሮ ከሚሠራበት ድርጅት የአንገት ማዕተቡን እንዲያወልቅ ተጠይቆ በመቃወሙ ምክንያት ከሥራ ገበታው እንደተሰናበተ ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ አስነብቧል።

ወጣቱን ቀጥሮ የሚያሠራው “ኢንግራም ማይክሮ” የተባለው ድርጅት “አንገት ላይ መስቀል ማድረግ ለደኅንነት አደገኛ ነው” ብሎ በማመኑ ወጣቱ መስቀሉን እንዲያወልቅ ቢጠይቀውም ወጣቱ በመቃወሙ ከሥራ ገበታው እንዳሰናበተው ከዘግባው ለመርዳት ተችሏል። በርካታ የእስልምና እምነት ተከታይ ጓደኞቹ ጀለቢያና ሂጃብ አድርገው እየሰሩ እርሱ ማዕተብ እንዳያደርግ መከልከሉ ሃይማኖታዊ መድሎ እንደተፈጸመበት መሆኑን ማስረዳቱን በዘገባው ተገልጧል።

የኩባንያው ባለሥልጣናት በበኩላቸው መስቀልም ሆነ ጌጣጌጥ ማድረግ እንደማይፈቀድ ለወጣቱ ማስረዳታቸውን ገልጸዋል። ጆርጅ በበኩሉ በድርጅቱ ተቀጥረው ያሉ ሠራተኞች ጌጣጌጦችንና የእስልምና አልባሳትን ለብሰው ሲሰሩ ማየቱን ገልጾ ‹‹በድርጅቱ ተቀጥረው ያሉ ሌሎች ብዙዎች ሂጃብ ለብሰው እንደሚሠሩት ሁሉ እርሱም የአንገት መስቀል በአንገቱ ላይ አድርጎ የመስራት መብት እንዳለው ለኩባንያው ባለሥልጣናት ማስረዳቱን ዘገባው አመላክቷል።

ባለፉት ዓመታት በምእራብ አውሮፓ ሀገራት በክርስቲያኖች ላይ በርካታ የሃይማኖት መድሎዎች መደረጋቸውን አስመልክቶ ሪፖርት መደረጉን ዘገባው አመልክቷል።



# ዓላማውን የሳተው የዐውደ ምሕረት ስብከታችን

ሠርክ ቃለ እግዚአብሔርን የምንሰማባቸው የቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረቶች እንደሰባክያኑ መልካቸው የተለያየ ነው። ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱት ቃለ እግዚአብሔርን ሰምተው ሊታነፁበት፣ ወደ ንስሓ ሊመለሱበት ፣ ባጠቃላይ የጽድቅ ሥራ ሊሠሩበት ነው። ዛሬ ዛሬ በየዐውደ ምሕረቶቻችን የምንሰማቸው አንዳንድ ስብከቶች ዓላማቸውን የሳቱ፣ በግለሰብ ፍላጎት እና ሐሳብ ላይ የተመሠረቱ ሆነዋል። በተከበረው የእግዚአብሔር ዐውደ ምሕረት ወንጌል መሰበክ ሲገባው ስለኳስ ጨዋታ፣ ስለሰባኪው የግል ዝንባሌና ምኞት፣ስለ ዘረኝነት ፣ ስለ ወቅቱ የሀገሪቱ የፖለቲካ ትኩሳት እንዲሁም ገንዘብ መሰብሰብ ላይ ያተኮረ መልእክት ማስተላለፍ የተለመደ ሆኗል። ከላይ ባነሳናቸው ሐሳቦች ዙሪያ ትኩረት የሚያደርጉ ምእመናንን ፍጹም የማያንፁ፣ በዓለማዊ ቋንቋና ሐሳብ የተሞሉ ፍጹም ግለሰባዊ ስብከቶች ከየዐውደ ምሕረቱ ሲሰሙ ሃይ የሚላቸውና ስሕተት ነው ባይ የላቸውም።

በአበይት በዓላት፣ በሠርክ ጉባኤና፣ በቅዳሴ ሰዓት የሚሰጡ ስብከቶችን ለመስማት የሚታደሙ ምእመናንም እንዲህ ዓይነት ከዓላማው የተፋታ ስብከት ሲሰሙ ለምን አይሉም። ነገሩን በውል ተረድተው ልክ አለመሆኑን ቢያውቁም በአብዛኛው ሰምተው እንዳልሰሙ፣ አይተው እንዳላዩ ወይም በይሉኝታና በፍርሃት ተይዘው እግዚአብሔርንም እንደመዳፈር ቆጥረውት ዝም ይላሉ። ግን እስከመቼ? ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ በመንግሥተ ሰማያት፣ በዘር ፣ በእርሾ እየመሰለ ማስተማሩን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

ዛሬ ዛሬ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሊቃውንት በተቀመጡበት ዐውደ ምሕረት በእነርሱ ፊት ወጥቶ የሚሰብከው ሰባኪ ከምእመኑ ጋር የማይገናኝ የምእመኑን ዕድሜ፣ የትምህርትና የኑሮ ደረጃዎች ፣ጾታንና የመሳሰሉትን ሁኔታዎች ያላገናዘበ ትምህርት ሲሰጥ ዝም ሊባል አይገባም። ምእመኑም የእግዚአብሔር ቤት ነው ብሎ አክብሮ የሚነገረውን ሰምቶ መሄዱ እንደተማረ ተቆጥሮ መታለፍ የለበትም። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት ስብከቶችን በክርስትናው ባልተለወጡ ምእመናን ሕይወት እያየነው ስለሆነ ነው። በተከበረው የእግዚአብሔር ዐውደ ምሕረት ላይ ወጥቶ ከምእመናን ልብ የማይደርስ ስብከት ሲሰጥ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ዝም ሊሉ አይገባም። የጉባኤው ተካፋይ ምእመንም ቢሆን እንዲህ ዓይነት ክፍተቶች ሲያይ ዝም ከማለት ወደ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር አለዚያም ወደ ስብከተ ወንጌል ኃላፊዎች ቀርቦ እንዲስተካከል ማድረግ ይጠበቅበታል።

አንዳንዱ ሰባኪ እንደ ተከበረው የእግዚአብሔር ቤት ዐደባባይ ሳይሆን እንደራሱ ቤት በሚቆጥረው መድረክ ላይ የመጽሐፍ ቅዱሱን ቃል ሳይሆን የራሱን ሐሳብ ብቻ ተናግሮ ይወርዳል። ምእመኑ ዘንድ ስለሚደርሰው የእግዚአብሔር ቃል ሳይሆን እርሱ በዚያች ሰዓት ስለሚያስተላልፈው ሐሳብ ብቻ ተጨንቆና ተጠቦ በመምጣት ያንኑ አስተላልፎ ሲወርድ ልክ አይደለህም ሊባል ይገባል። እንዲህ ዓይነቱ ሰባኪ ሲያጠፋ ስላልተነገረው ብቻ ራሱን ትክክል አድርጎ በየሄደበት ዐውደ ምሕረት ከምእመናን ሕይወት ያልተገናኘ ስብከት ሲሰብክ ይኖራል። በተሳሳተበት ቀንና ቦታ ስላልተነገረውም ከመንገድ የወጣ ትምህርቱ ሥር እየሰደደ ይሄድና ለመመለስ ይቸግራል። ‹‹ ሳይቃጠል በቅጠል›› እንዲሉ አባቶች ገና ከመነሻው ያልተነገረ ጥፋት በአድራጊው ዘንድ እንደ ትክክል ይቆጠራልና ሰባኪውም ሆነ ምእመኑን ወደ ፍጹም ስሕተት ሳይገቡ እርምት ሊሰጥ ይገባል።

የዐውደ ምሕረቱ አስተባባሪ ወይም ፕሮግራም መሪ ‹‹እከሌ የተባሉት መምህር አሁን ያስተምሩናል›› ብሎ ለወንጌል ትምህርት የተፈቀደለትን መድረክ ተጠቅሞ እግዚአብሔርን ሳይሆን ራሱን የሚያስተዋውቀውን፣ቃለ ወንጌልን ሳይሆን ይዞት የመጣውን መጽሐፍ ወይም ሲዲ አስተዋውቆና በረከት የሚገኘው ከመጽሐፉና ከሲዲው ነው በማለት የወንጌሉን ቃል ወደ ጎን ሲተው ሃይ ባይ የሚገሥፅ ያስፈልጋል። ዐውደ ምሕረቱ ለቃለ ወንጌሉ ነው በማለት ከስሕተቱ እንዲታረም ማድረግ ካልተቻለ

‹‹ቤቴን የንግድ ቤት አደረጋችሁት . . . ›› እንዳለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዐውደ ምሕረቱ ወደ ንግድ ማዕከልነት ሳይለወጥ በጊዜ መላ ሊበጅለት ይገባል፡፡

ትናንት ያየውን ዜናና ዓለማዊ ፊልም ለስብከቱ ማዳመቂያ አድርጎ መድረክ ላይ የሚወጣውም ሰባኪ መንፈሳዊ ዕውቀትን ለመገብየት የመጣውን ምእመን ስላየው ዜናና ፊልም ዳግም እየነገረ የቤተ ክርስቲያንን ክብር ስለሚያዋርደው ሰባኪ አንድ ነገር ሊባል ይገባል፡፡ በዐውደ ምሕረቱ ያልተለመደ ፌዝና ስላቅ እያስተላለፈ ምእመኑን ‹‹ይሄ ነው ትክክለኛው›› እንዲሉ መንገድ የሚጠርገውን ሰባኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከዐውደ ምሕረቷ ዘወር ልታደርገው ይገባታል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ልጆችም ቢሆኑ እንዲህ ዓይነት ቀልድና ፌዝ ከቃሉ ጋር ተቀላቅለው ሲነገሩ፣ ዓለምን ከነኮተቷ ወደ ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ሊያስገቡ ሲሞክሩ ‹‹ይህ የአባቶቻችን ትምህርት አይደለም›› በማለት ለቤተ ክርስቲያናቸው ክብር ሊቆረቆሩ ይገባል፡፡

ቃለ እግዚአብሔርን ለመስማት ፣ መንፈሳዊ ዕውቀቱን ለማሳደግ በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ውስጥ ለተሰበሰበ ምእመን የተነሣበትን ርእሰ ጉዳይ ትቶ ከርእሱ ወጥቶ ወይም የሆነው ያልሆነውን ሲዘባርቅ የዕለቱንም በዓል አስመልክቶ አንድም ሳያስተምር የጉባኤውን ሰዓት የሚጨርስ ራሱን እንዲያስተካክል መንገር ከቤተ ክርስቲያን አባቶችም ሆነ ከምእመናን ይጠበቃል፡፡ ጊዜውን ተጠቅሞ ለምእመኑ ማስተላለፍ ያለበትን መንፈሳዊ መልእክት ሳያስተላልፍ ፣ ምእመኑን መጀመሪያ ላይ የሰማው ርዕሰ ጉዳይ እስኪጠፋበት እና አንድም ፍሬ ነገር የማያገኝበትን እንቶ ፈንቶ ሲያወራ ቆይቶ ከመድረክ ላይ የሚወርደውን ሰባኪ ተብዬ ‹‹ ቃለ ሕይወት ያሰማልን›› ማለት ሳይሆን ከሕስተቱ ተምሮ እንዴት ማስተማር እንዳለበት አቅጣጫ መስጠት ተገቢ ነው፡፡

ታላላቅ በዓላት በሚከበሩባቸው አብያተ ክርስቲያናት ዐውደ ምሕረት ላይ ምእመኑን ‹‹ ዕልል በሉ፣ አጨብጭቡ›› ከማለት ያለፈ ስለ ዕለቱ አንድም ነገር ሳይናገሩ ከመድረኩ ለሚወርዱ ሰባኪዎቻችን አስቀድሞ ርእስ እና አቅጣጫ መስጠት ተገቢም ነው፡፡ የዕለቱን ክብረ በዓል ምንነት ለምእመናን ከማስተማር ይልቅ ገንዘብ ስለመለመን ብቻ አውርተው የሚወርዱ ሰባኪዎቻችን በምእመኑ እንደበት ሳይቀር ‹‹ ምን እነሱ ብር መለመን ብቻ ነው›› እስከመባል ደርሰዋልና ቤተ ክርስቲያን ይህን ልታስብበት ይገባል፡፡

የቤተ ክርስቲያን አምባሳደር ሆነው በቆሙበት መድረክ ላይ የወንጌልን ቃል ሳይሆን ዘረኝነትን የሚዘሩ፣ ዘለዓለማዊ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ከማስተላለፍ ይልቅ ሰሞነኛ የፖለቲካ ትኩሳት ማቀንቀን የሚቀናቸው ሰባክያንን ‹‹ቦታው እዚህ አይደለም›› በማለት ወደ ትክክለኛው መሥመር እንዲገቡ ማድረግ ከቤተ ክርስቲያን ልጆች ይጠበቃል፡፡ ሞልቶ ከተረፈው የእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ከዓለም በቃረሙት ቃላትና ምሳሌ ወደ ዐውደ ምሕረት አምጥተው ምእመናንን የሚያደነቁሩ ሰባክያን ልክ አይደለም ሊባሉ ይገባል፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የአለባበስ ሥርዓት በመጣስ ያልተፈቀደላቸውንና የማይገባቸውን የቤተ ክርስቲያን ልብስ በመልበስ ወደ መድረክ ብቅ የሚሉ ሰባኪዎቻችንን ቤተ ክርስቲያን ችላ ልትላቸው አይገባም፡፡

ዐውደ ምሕረቱን ተጠቅመው የእግዚአብሔርን ቃል የሚሸቃቅጡትን፣ ‹‹ በነፃ የተሰጣችሁን በነፃ ስጡ ›› የሚለውን ቃል ዘንግተው ኪሳቸውን ለመሙላት ብቻ የምእመኑን ኪስ የሚያራግፉትን (ዋጋ ተምነው ይህን ያህል ሊከፈለኝ ይገባል በማለት በድርድር ዐውደ ምሕረት ላይ የሚቆሙ) ሰባክያን ቤተ ክርስቲያን ለይታ ልታወጣቸው ይገባል፡፡ በዚያው ልክ ለቤተ ክርስቲያን ክብር የቆሙ ጨዋ የወንጌል ሰባክያንን (ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ደሃ አይደለችምና) ወደ መድረክ ልታመጣ ፣ ልትጋብዝ፣ እንዲያስተምሩ ልታደርግም ይገባል፡፡ ባጠቃላይ ምእመኑ ጥሎት የመጣውን ዓለም በቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረት ላይ በድፍረት የሚያስተዋውቁ የወንጌል ነጋዴዎች ቤተ ክርስቲያንንም ሆነ ምእመኑን እየጎዱ ነውና ቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረቷን በትኩረት ልታየው ይገባል፡፡



ቅዱስ ፓትርያርኩ ከድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ አባላት ጋር

# ቤተ ክርስቲያንን ያከበረች ከተማ...

በካሣሁን ለምለሙ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ፈተና ያልተለያት እንደሆነች በዘመናት ውስጥ ከተጻፉ የታሪክ ድርሳናት መረዳት ይቻላል። ቤተ ክርስቲያን በፀረ ክርስቲያን ኃይሎች መፈተኗ አላጠፋትም፤ ምእመናንንም ከአምልኮተ እግዚአብሔር አላራቃቸውም። ይልቁንም ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልእኮዋን እያሰፋች ለዓለም ብርሃን መሆኗን ቀጥላለች። ከዘመናዊ ትምህርት ዘርፉ ከሚገኝ ዕውቀት በበለጠ የቋንቋ፣ የሥነ ጥበብ፣ የኪነ ሕንፃና የፍልስፍና ምንጭ ሆና መቀጠሏ ዓለም ያወቀው ገሃድ ነው። ይሁን እንጂ ኃያልነቷንና ታሪካዊነቷን የተረዱና ያልተረዱ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ሌት ተቀን ከሚያልሙ ፀረ ክርስቲያን ኃይሎች መገኛ ሀገራት መካከል ሀገራችን ኢትዮጵያ አንዷ ናት።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር ከመሆኗ ጋር ተያይዞ በሰላምና በፍቅር ተከባብሮ አብሮ በመኖር የዓለም ተምሳሌት ብትሆንም በጉያዋ የበቀሉ አንዳንድ እሾሆች ግን ቤተ ክርስቲያንን ሲወጓት ይስተዋላሉ። እነዚህ ኃይሎች ቤተ ክርስቲያንን ለመውጋታቸው መነሻ ምክንያት ምንድነው ብለን ስንጠይቅ በስሑት ትርክት ተነሣሥተውና ‹‹የእኛ›› የሚሉትን ሃይማኖት በሌላው ላይ ለመጫን በማለም እንደሆነ ድርጊታቸው ይመሰክራል። ከዚህም ባሻገር በሀገሪቱ ኦርቶዶክሳዊ ዕሤቶቻችን በማጥፋት የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ለማዳከምና የማትጠፋውን ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ይታትራሉ።

የጥፋት ኃይሎች የጥፋት እጃቸውን በመላው ኢትዮጵያ ባሉ ኦርቶዶክሳውያ ክርስቲያኖች ላይ የሚሰነዝሩ ቢሆኑም በተለይ ግን ሕዝበ ሙስሊሙ በሚበዛባቸው አካባቢዎች ማለትም በሶማሌ፣ በሐረሪ እና በኦሮምያ ክልሎች፣ በድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር እና በአማራ ክልል የኦሮሞ ልዩ ዞን አካባቢዎች ለክርስቲያኖች የሥጋት ቀጠናዎች ሆነው ቆይተዋል። በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ከጥንት እስከዛሬ አልፎ አልፎ በእምነታቸው ምክንያት በግፍ ሲገደሉ፤ ሃይማኖታቸውን ተገደው እንዲቀይሩ ሲደረግ፤ ሀብት ንብረታቸው ሲዘረፍ ሲቃጠል እንዲሁም ከማኅበራዊና ፖለቲካዊ አደረጃጀቶች ሆን ተብሎ እንዲገለሉ ሲደረግ ቆይቷል።

በቅርቡ እንኳን በ፳፻፲፪ ዓ.ም በርካታ ኦርቶዶሳውያን ክርስቲያኖች በእምነታቸው ምክንያት ብዙ ዋጋ ከፍለዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ለሚመለከተው አካል አቤቱታ ብታቀርብም ችግሩ ከመስፋቱ ውጭ ተጨባጭ መፍትሔ ሳታገኝ በርካታ ጊዜያት አልፈዋል፡፡

ነገር ግን አንዳንድ አካባቢዎች የመንግሥትን ማስጠንቀቂያና የቤተ ክርስቲያንን አቤቱታ አድምጠው ችግሩን በሂደት ያስተካከሉ መኖራቸውን መናገር ተገቢ ነው፡፡ ከእነዚህ አካባቢዎች መካከል የሶማሌ እና የሐረሪ ክልሎች እንዲሁም የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ይገኙበታል፡፡ ሌሎቹን በሌላ ጊዜ የምናነሣቸው ሆኖ የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር ከጊዜ በኋላ ለኦርቶዶክሳውያንና ለቤተ ክርስቲያን ሰላምና ደኅንነት መጠበቅ ያበረከተውን አስተዋጽኦ ተከትሎ ቤተ ክርስቲያን ስለሰጠችው ዕውቅና በአጭሩ የምንቃኝ ይሆናል፡፡ እንደሚታውቀው በድ ሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ምእመናን የዐደባባይ በዓላትን በነፃነት የማያከብሩበት፤ ሥርዓተ አምልኳቸውን በነፃ የማይፈጽሙበትና ከማኅበራዊና ፖለቲካዊ አደረጃጀቶች የተገለሉበት እንደነበር በተለያዩ ጊዜያት ሰምተናል፤ ዓይተናልም፡፡ ነገር ግን ከቅርብ ጊዜያት በኋላ ከተማ አስተዳደሩ ባስቀመጠው ቁርጠኛ አቅጣጫ የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን መብትና ደኅንነት እንዲከበር ተደርጓል፡፡

ይህም በመሆኑ የምእመናን የደኅንነት ሥጋት ተቀርፏል፤ የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ጥያቄዎች ተመልሰዋል፤ እንዲሁም የአባቶችና የምእምና ተቀባይነትና አካባቢያዊ ተሳትፎ ጨምሯል፡፡ ይህንን መልካም ሥራ በአንክሮት የተመለከተው የድሬ ዳዋ ሀገረ ስብከት በቤተ ክርስቲያን ደረጃ የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር ዕውቅና እንዲሰጠው በወሰነው መሠረት ጉዳዩን ለጠቅላይ ቤተ ክህነት አቅርቦ የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ከነ ሙሉ ካቢኒያቸው (የሥራ ባልደረቦቻቸው) በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የምስጋናና ዕውቅና መርሐ ግብር ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ በዚህ የዕውቅናና የምስጋና መርሐ ግብር ቅዱስ ፓትርያርኩን ጨምሮ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ሙሓዘ ጥበባት ዲ/ን ዳንኤል ክብረት (የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማኅበራዊ ዘርፍ አማካሪ) ተገኝተዋል፡፡

በመርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሳነ ሊቃ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር ለቤተ ክርስቲያን እያደረገ ባለው ሁለንተናዊ ድጋፍ የመልካም ተምሳሌት መሆኑን ገልጠዋል፡፡ ከተማ አስተዳደሩ ለቤተ ክርስቲያን ያበረከተው አስተዋጽኦ ለሌሎች ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አርአያ ሊሆን እንደሚችል የተናገሩት ቁድስነታቸው አብዛኛው የከተማ አስተዳደሩ አመራሮች ከኦርቶዶክስ እምነት ውጭ መሆናቸውን ጠቅሰው የሃይማኖት ልዩነት ቢኖረንም ፍቅራችንና አንድነታችንን አያሳሳውም ኢትዮጵያዊነታችንም አያጠፋውም ብለዋል፡፡

ሀገራችን የጋራ እስከሆነች ድረስ ሁሉም ዜጎች ሰብአዊ መብታቸው ተከብሮላቸው በጋራ በአንድነትና በፍቅር ሊኖሩ ይገባል ሲሉም አስረድተዋል፡፡ ቅዱስ ፓትርያርኩ አክለውም ‹‹አንድነታችንና ፍቅራችንን ልንጠብቀው የሚገባው በሃይማኖት፣ በዘርና በቀለም ሳንለያይ ከሆነ ብቻ ነው›› ብለዋል፡፡ የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር የሰላምና የልማት ተምሳሌት መሆኑ አመራሮቹ ደስ ሊላቸው ይገባል ካሉ በኋላ ሁሉም የሀገራችን የፖለቲካ አመራሮች የመልካም ሥራ ምሳሌዎችን በመውሰድ ለእውነትና ለሀገር አንድነት እንዲሠሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የድሬ ዳዋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ቀሲስ ማትያስ በቀለ በመርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልእክት የድሬ ዳዋ ሀገረ ስብከት ላለፉት ሦስት ዓመታት ከፍተኛ የሆነ ሁከትና ብጥብጥ ያስተናገደ አካባቢ እንደነበረ አስታውሰው ኦርቶዶኮሳውያን ምእመናን በነፃነት የማያመልኩበትና የዐደባባይ በዓላትንም በሥጋት የሚያከብሩት ወቅት እንደነበረ ተናግረዋል፡፡ ነገር ግን አሁን ያሉት የከተማ አስተዳደሩ አመራሮች ቁርጠኛ በመሆናቸው በሰላምና ልማት ዙሪያ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተቀራርበው እየሠሩ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን በምታደርገው የሰላምና የልማት እንቅስቃሴ ሁሉ ከተማ አስተዳደሩ ድጋፍ ማድረጉን ያነሡት ሥራ አስኪያጁ ለዚህ መልካም ሥራቸውም በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የዕውቅናና የምስጋና መርሐ

ግብር እንደተዘጋጀላቸው አንሥተዋል፡፡ ከተማ አስተዳደሩ ለቤተ ክርስቲያን ተጨማሪ ይዞታዎችን ከመስጠት ባሻገር የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ለሌላቸው የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎችም የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ሠርቶ እንደሰጠም ሥራ አስኪያጁ በዕለቱ አስታውቀዋል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቤቶችና ሕንፃዎች አስተዳደርና የልማት ድርጅት ኃላፊ አፈ መምህር አባ ገብረ ሥላሴ በበኩላቸው ከዚህ ቀደም በድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር ተወርሰው የተመለሱ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች እንዳሉ ጠቅሰው ከውርስ ከተመለሱት ቦታዎች መካከል በአንዱ ላይ የገቢ ማስገኛ ሕንፃ ለመሥራት ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በቅዱስ ፓትርያርኩ አማካይነት የመሠረት ድንጋይ እንደተቀመጠ ተናግረዋል፡፡

የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ አሕመድ መሐመድ ቡህ ለከተማ አስተዳደራቸው ቤተ ክርስቲያን የሰጠችው ዕውቅና እንዳስደሰታቸው ገልጠው ይህም በቀጣይ ለሌላ መልካም ሥራ እንዲነሣሡ እገዛ እንደሚያደርግላቸው ተናግረዋል፡፡ ሌላው በመርሐ ግብሩ የተገኙት የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ልዩ አማካሪና የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር የብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ መብራት ገብረየስ በበኩላቸው ቤተ ክርስቲያን ለሀገራችን የኪነ ሕንፃ ጥበብ ዕድገት ያበረከተችውን አስተዋፅኦ አድንቀው ለተደረገላቸው መስተንግዶ፣ አቀባበልና ዕውቅና ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

የቤተ ክርስቲያንን ጥንታዊትና ዓለም አቀፋዊነት በመረዳት በሀገራችን ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ መደበኛና ኢመደበኛ አደረጃጀቶች ተገቢውን እውቅናና ድጋፍ በመሥጠት ቤተ ክርስቲያን ለሀገርና ለወገን ያበረከተችውንና እያበረከተች ያለውን አስተዋፅኦ እንድትቀጥልበት ማድረግ ይገባል፡፡ በሌሎች የሀገራችን ክፍሎች የምትገኙ የፖለቲካ አመራሮችና ቡድኖች የድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር የመልካም ሥራ ተሞክሮን በመመልከት ለቤተ ክርስቲያን ሁሉን አቀፍ እገዛና ትብብር ልታደርጉ ይገባል እንላለን፡፡

**የድሬ ዳዋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ቀሲስ ማትያስ በቀለ በመርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልእክት የድሬ ዳዋ ሀገረ ስብከት ላለፉት ሦስት ዓመታት ከፍተኛ የሆነ ሁከትና ብጥብጥ ያስተናገደ አካባቢ እንደነበረ አስታውሰው ኦርቶዶኮሳውያን ምእመናን በነፃነት የማያመልኩበትና የዐደባባይ በዓላትንም በሥጋት የሚያከብሩት ወቅት እንደነበረ ተናግረዋል። ነገር ግን አሁን ያሉት የከተማ አስተዳደሩ አመራሮች ቁርጠኛ በመሆናቸው በሰላምና ልማት ዙሪያ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተቀራርበው እየሠሩ እንደሆነ አስረድተዋል።**

# «የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ ነው ያኖረኝ»

***መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ አእምሮ ብሩ***

***ክፍል አንድ***

**በመጽሐፈ ሲራክ**

***የተወደዳችሁ አንባብያን በዛሬው የቤተ አብርሃም ዐምድ ዝግጅታችን የምናቀርብላችሁ በደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ካተድራል የሐዲስ ኪዳን መምህር የሆኑትን መጋቤ ሐዲስ አባ አእምሮ ብሩን ነው። በ ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ወደ ካቴድራሉ ሲመጡ በሐዲስ ኪዳን መምህርነት ተመድበው ለተወሰነ ጊዜ አገልግለዋል። ብዙም ተማሪዎች በቦታው ላይ ባለመገኘታቸው በአሁን ሰዓት በስብከተ ወንጌል እና በተጓዳኝ መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ይገኛሉ። ከዚህም በተጨማሪ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል እና የማይክሮ ሊንክ ግቢ ጉባኤዎችን እንዲሁም በአጥቢያው ዙሪያ የሚገኙ የመንግሥት እና የግል መሥሪያ ቤት ሠራተኞችን ከማኅበረ ቅዱሳን ጋር መበሆን ያስተምራሉ፣ የአጥቢያውን ሕፃናት ጠዋትና ማታ ከፊደል ጀምሮ እያስተማሩ ይገኛሉ። አባታችን ከልጅነታቸው ጀምሮ ያላቸውን የአገልግሎትና የሕይወት ተሞክሮ እንዲያካፍሉን እንግዳ አድርገናቸዋል ተከታተሏቸው፦***

***ስምዐ ጽድቅ፦*** አባታችን ከእርስዎ ጋር ይህን ቃለ መጠይቅ እንድናደርግ ስለፈቀዱልን ከልብ እናመሰግናለን። እስኪ የልጅነት ሕይወትዎን ይንገሩን? የት ተወለዱ? የእናትና የአባትዎ ስም ማን ይባላሉ?

***መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ አእምሮ ብሩ፦*** እኔም ይህን ቃለ መጠይቅ እንዳደርግ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ። በርግጥ መነኩሴ እንኳ ሀገር አለኝ ማለት የለበትም ሆኖም ለእናተ ዓላማ የሚጠቅማችሁ ከሆነ የተወለድኩት ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ.ም በጎንደር ክፍለ ሀገር (ደቡብ ጎንደር) ልዩ ስሙ የሾ ሚካኤል ከሚባል አጥቢያ ነው። አባቴ ቄስ አስረስ መኮንን ይባላሉ እናቴ ወ/ሮ የሺመቤት ብሩ ትባላለች እኔ የምጠራው በእናቴ አባት ስም ነው። የሚተዳደሩት በግብርና ነው።



**መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ አእምሮ ብሩ**

***ስምዐ ጽድቅ ፦*** እስኪ ስለ አብነት ትምህርት ቤት ሕይወትዎ ይንገሩን የአብነት ትምህርት የት የት ተማሩ?

***መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ አእምሮ፦*** ትምህርት ቤት የገባሁት በልጅነቴ ነው ዓመተ ምሕረቱን አሁን ላይ አላስታውስም። ትምህርት የጀመርኩት ከዚያው ከትውልድ ሀገሬ ደቡብ ጎንደር የሾ ሚካኤል ነው። ከፊደል አንስቶ እስከ ዜማ የተማርኩት ከዚያ ነው። ያስተማሩኝ መሪጌታ ውበቱ አድማሴ ይባላሉ። ትምህርቱን እንደጨረስኩ ከአቡነ ዜና ማርቆስ (አሁን አርፈዋል) ዲቁናን ተቀብያለሁ። በዲቁና ትንሽ ካገለገልኩ በኋላ መጀመሪያ የሔድኩት ወደ ደቡብ ጎንደር እስቴ መካነ የሱስ ደብረ ሃይማኖት ደብር ነው። አካሄዴ ከታላቁ መምህር ከመጋቤ ሐዲስ አባ ኃይለ ሚካኤል ዘንድ ሐዲሳትን ለመማር ነበር።

መጽሐፍ አስተምሩኝ ብዬ ወደ እርሳቸው ሄድኩ እንዳገኙኝ ‹‹ቅኔ ተምረሃል ወይ?›› ብለው ጠየቁኝ:: አልተማርሁም አልኳቸው እሳቸውም ቅኔ ካልተማርህማ መጽሐፍ ሊሆንህ አይችልም መጀመሪያ ሂድ ቅኔ ተቀኝተህ ና አሉኝ:: እኔም ቃላቸውን ተቀብዬ እንዳሉኝ ሁለት ዓመት ቅኔ ቤት ቆየሁ:: መጀመሪያ እዚያው ደቡብ ጎንደር ከሚገኙት መሪጌታ ነገድ ተማርሁ፤ሁለተኛ ሞጣ ጊዮርጊስ ከነበሩት አንጋፋው መምህር ገብረ ሥላሴ (አሁን ሰዋሰወ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ ነው ያሉት) ተማርሁ:: ቅኔ ተቀኝቼ ሳበቃ ተመልሼ ወደ ደቡብ ጎንደር እስቴ መካነ የሱስ ደብረ ሃይማኖት ታላቁ ደብር ከሚገኙት መጋቤ ሐዲስ መምህር ኃይለ ሚካኤል ዘንድ መጽሐፍ ጀመርኩ ማለት ነው እሳቸውም ተቀብለው ሐዲሳቱን አስተማሩኝ::

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ምንኩስናን የት እና ከማን ተቀበሉ?

***መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ አእምሮ፦*** ምንኩስናን የተቀበልኩት ሐዲሳትን ከተማርኩበት ታላቁ ደብር እስቴ መካነ የሱስ ደብረ ሃይማኖት ደብር ከመምህሬ ከመጋቤ ሐዲስ አባ ኃይለ ሚካኤል ነው:: መጋቤ ሐዲስ በአካባቢው የሚታወቁ እና የሚከበሩ ታላቅ ሊቅ ናቸው:: በሕይወቴ በትምህርት ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወትም አብነት የምላቸው እሳቸውን ነው:: በተለይ በምንኩስናው ዓለም ከትምህርቱ ያላነሰ የሕይወት ትምህርት ነው ከእርሳቸው አግኝቻለሁ::

ምንኩስናውን በኅዳር ወር ፲፱፻፹ ዓ.ም ተቀብዬ ወዲያው በታኅሣሥ ወር የቅስናን መዓረግ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ (ያኔ የጎንደር ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ ነበሩ) ተቀበልኩ:: መዓረገ ቅስናን እንደተቀበልኩ ወዲያው ወደ ሰሜን ጎንደር መንበረ መንግሥት ነው የሄድኩት:: አካሄዴም ብሉይ ኪዳንን ለመማር ነው:: ጎንደር መንበረ መንግስት መድኃኔ ዓለም አራቱ ጉባኤ ቤት ሄጄ ከሊቀ ሊቃውንት መንክር መኮንን ዘንድ (ዛሬ ሊቀ ሊቃውንት እዝራ የያዙትን ማለት ነው) ብሉይ ኪዳንን ማለትም ዳዊት ትርጓሜን ተማርኩ ሌሎች የጨመርኳቸውም አሉ:: እሱን በጉባኤ እያካሄድኩኝ በትርፍ ጊዜዬ ደግሞ ፋሲል ግንብ አጠገብ ከሚገኝ አደባባይ ኢየሱስ ከሚባል ትልቅ ቦታ መሪጌታ ፅጌ ከሚባሉ መምህር ደብረ አባይ ቅዳሴን ቀጽያለሁ::

***ስምዐ ጽድቅ፦*** የአብነት ትምህርት ቤት ሕይወትን እንዴት ይገልጹታል?

***መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ አእምሮ፦*** የአብነት ትምህርት ቤት ወይም የቆሎ ትምህርት ቤት ሕይወት ፈተናው ከባድ ነው:: በእውነት ተስፋ የሌለው ሰው ሁሉ በተስፋ መንቀሳቀስ አለበት:: እኔ በነበርኩበት ዘመን አብነት ትምህርት ቤት እጅግ በጣም ችግር የበዛበት ነበር:: ለመማር ችግሩም ረሀቡን፣ ጽሙን፣ መታረዙን ሁሉ በትእግስት ማለፍ ነበረብን:: በጊዜው በአብነት ትምህርት ቤት ብዙ ችግር አሳልፈናል::

አሁን ላይ ሁኜ ሳስበው ‹‹ያን ጊዜ የኔ ኃይል ነው እንዴ? አይደለም የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ ነው ያኖረኝ›› ነው የምለው:: እዚህ ለመዘርዘር ጊዜና ቦታ የማይበቃው ብዙ ችግር ነው ያሳለፍነው:: ለምሳሌ በዚያን ጊዜ ልብሳችን አንድ አንሶላ እና አንድ ቁምጣ ብቻ ነበረ ቅያሪም የለንም ቀን ለብሰን እንውላለን እስዋኑ ደግሞ ለሌት አድርገ ነው የምንተኛው:: ያን ጊዜ የከበደ ወቅት ነበር ማለት ነው:: በምግቡም በኩል እንደዚያው ነው ልመና ተወጥቶ ከውሻ ታግሎ የሚገኘው ነገር ጥሬ ከፍ ካለም ወጥ የለው ለምለም እንጀራ ነው:: በዚያ ላይ በሽታ አለ ፣ ያን ሁሉ ተቋቁሞ ነው በአብነት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚኖረው::

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በአብነት ትምህርት ቤት ሕይወት ውስጥ ውጣ ውረዱ እንዳለ ሆኖ ምን ያስደስቶታል?

***መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ አእምሮ፦*** እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ከቤተሰብ ተለይቶ ርቆ በመሄድ የሚገኘው መንፈሳዊ እውቀት ነፍስን ያለመልማል ልብን ደስ ያሰኛል:: በአብነት ትምህርት ቤት ሕይወቴ የምደሰትበት እሱ ነው::

ሌላው የሚያስደስተኝ እስቴ መካነ ኢየሱስ እያለሁ አራቱን ወንጌላውያን ትርጓሜ በእጄ መገልበጤ ነው።   ቀለም በጥብጬ ብዕር ቀርጬ ደብተር አስምሬ በመጻፌ ትዝ የሚለኝና የሚያስደስተኝ ትልቁ እሱ ነው ማለት ነው፡

እስቴ መካነ ኢየሱስ ከጉባኤ ቤት እያለሁ ወዲያው እንማራለን ጉባኤ ያሄዱልናል የተተረጎመልንን ወጥተን እንጽፋለን። የምንጽፍበትን ደብተር የምንገዛው ደግሞ የቀን ሥራ ሠርተን በምናገኘው ገንዘብ ነው።  የሚሠራው ስራ አጨዳ ነበር ለእርሱ የሚከፈለን አንድ ብር ነው።  አንድ ብር አራት ደብተር ይገዛል በዚያ ላይ ነው የወንጌላቱን ትርጓሜ ጽፌ የጨረስኩት።  ከእስቴ ስወጣ ጽፌ ደጉሼ ነው የወጣሁት።  ከአራቱ ወንጌላውያን ውጪም የጻፍኳቸው አሉ። ለምሳሌ ቅዳሴ ማርያም ውዳሴ ማርያም፣ ኪዳን፣ ባህረ ሃሳብ እነዚህን ሁሉ ጽፌ ነው የወጣሁት።

ዐይኔ እንደምታዩው የተፈጥሮ አይደለም ያን ጊዜ የተጎዳ ነው።  አሁን በሀገራችን ፀሐፍያን ስንክሳር፣ ተአምረ ማርያም፣ ገድልን በብራና ሲጽፉ ለዐይናቸው ጥንቃቄ ያደርጋሉ።  ከራሳቸው ላይ ቅቤ አድርገው ጥሩ ነገር እየበሉ ጥሩ ነገር እየጠጡ ነው የሚጽፉት፤ እኛ ግን በደረቁ ደረቅ ገብስ እየበላን ከተሻለ ደግሞ ከሳምንት አንድ ቀን ቁራሽ ይገኛል ለምለም እንጀራ መቼም አይታሰብም ያን እየበላን ነበር የምንጽፈው።  የአብነት ትምህርት ቤት ፈተናው ብዙ ነው ስል ይህን ሁሉ ጨምሮ ነው። አሁን ላይ ሆኜ ያን ሁሉ ጽናትና ብርታት ያን ሁሉ ተስፋ እንድንችል አድርጎ ለዚህ ስላበቃኝ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለው።

ያው ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት በእስቴ ጉባኤ ቤት ከትምህርቴ ጎን ለጎን ከላይ የጠቀስኩዋቸውን መጻሕፍት ከገለበጥኩ በኋላ ከመምህሬ ከመጋቤ ሐዲስ አባ ኃይለ ሚካኤል አቡነ ዘበሰማያት ተቀብዬ ብሉይ ኪዳንን ለመማር ሰሜን ጎንደር መንበረ መንግሥት መድኃኔ ዓለም አራቱን ጉባኤ ቤት ነው የሔድኩት።

***ስምዐ ጽድቅ*** ፦ በጎንደር መንበረ መንግሥት መድኃኔ ዓለም አራቱ ጉባኤ ቤት የዳዊት ትርጓሜን እንዲሁም ሌሎች ትምህርቶችን መማርዎን ፤ በትርፍ ሰዓትዎ ደግሞ በአደባባይ ኢየሱስ ደብረ አባይ ቅዳሴን መቀጸልዎትን ነግረውኛል እዚያ ምን ያህል ጊዜ ቆዩ ምንስ ሠሩ?

***መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ አእምሮ፦*** በጎንደር መንበረ መንግሥት መድኃኔ ዓለም ብዙ አልቆየሁም በ፲፱፻፹፰ ዓ.ም በምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት የናዝሬት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ በስብከተ ወንጌል እና በመጽሐፍ መምህርነት እንዳገለግል በደብዳቤ ተመድቤ ወደዚያው ሄድኩ።   እዚያ ለአራት ዓመታት አገልግያለሁ ያን ጊዜ ይሄን ያህል ሰውም አልነበረበትም፤ነገርግን እዚያ የቆየሁባቸው አራት አመታት ትልቅ አገልግሎትም የሰጠሁበትም ነበረ።

**የምንጽፍበትን ደብተር የምንገዛው ደግሞ የቀን ሥራ ሠርተን በምናገኘው ገንዘብ ነው። የሚሠራው ስራ አጨዳ ነበር ለእርሱ የሚከፈለን አንድ ብር ነው።  አንድ ብር አራት ደብተር ይገዛል በዚያ ላይ ነው የወንጌላቱን ትርጓሜ ጽፌ የጨረስኩት።  ከእስቴ ስወጣ ጽፌ ደጉሼ ነው የወጣሁት።  ከአራቱ ወንጌላውያን ውጪም የጻፍኳቸው አሉ። ለምሳሌ ቅዳሴ ማርያም ውዳሴ ማርያም፣ ኪዳን፣ ባህረ ሃሳብ እነዚህን ሁሉ ጽፌ ነው የወጣሁት።**

# “የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ሥራ መሆን ያለበት የልጆቿን ሰላምና ደኅንነት ማስጠበቅ ነው”

*-ብፁዕ አቡነ አብርሃም (የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)*

**ክፍል አንድ**



*ብፁዕ አቡነ አብርሃም*
*(የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)*

*በካሣሁን ለምለሙ*

በፀጥታ መደፍረስ ምክንያት ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ተፈናቅለው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አዊ ብሔረሰብ አስተዳድር ቻግኒ ከተማ ዙሪያ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠልለው ይገኛሉ፡፡ የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም እነዚህን የኅብረተሰብ ክፍሎች ለማጽናናት፣ ለመባረክ እንዲሁም ከሀገረ ስብከቱ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ርዳታ ለማስረከብ በቦታው በተገኙበት ወቅት ከማኅበረ ቅዱሳን ቴሌቪዥን ጣቢያ ጋር ያደረጉትን አጭር ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባባ፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በፀጥታ ችግር ምክንያት ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ተፈናቅለው በአማራ ክልል ቻግኒ ከተማ ዙሪያ የተጠለሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ሲያዩ ምን ተሰማዎት? ምንስ ታዘቡ?

***ብፁዕ አቡነ አብርሃም፡-*** ቻግኒ ላይ ያየሁት ሁኔታ እጅግ አሳዛኝና ልብን የሚሰብር ክስተት ነው፡፡ ከፖለቲካ የራቁና ሠርቶ አርሶ ከመብላት ውጭ ምንም የማያውቁ ዜጎችን ከሞቀ ቤታቸው እያስወጡ በጭካኔ መግደልና ማሳደድ በእውነት ሰብአዊነትን ያላከበረ ተግባር ነው፡፡ ምንም የማያውቁ ሕፃናት፣ ለዘመናት ሀገራቸውን በተለያየ መስክ ያገለገሉ የዕድሜ ባለጸጎች ሴቶችንና እናቶችን ጭካኔ በተሞላበት መንገድ መግደልና ማፈናቀል የወንድነት መለኪያ መስፈርት ሊሆን አይገባም፡፡ ከሞት ጥላ አምልጠው በቻግኒ ከተማ አቅራቢያ ተጠልለው ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች የቀን ፀሐይ የማታ ብርድ እየተፈራረቀባቸው ማየት ደግሞ ከምንም በላይ ልብን ያቆስላል፡፡

ይህን ግፍ አይቶ የማያወግዝና በቃ የማይል አካል ካለ ሰውነቱ ያጠራጥራል፡፡ እኔ እንደ ሃይማኖት አባትነቴ በቦታው ተገኝቼ ጉዳት የደረሰባቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች በማፅናናቴና አባታዊ ቡራኬ በመስጠቴ እጅግ ደስ ብሎኛል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ያየሁት ሁኔታ እጅግ ልቤን የሰበረውና ምን ልሠራ እንደሚገባኝ የቤት ሥራ የሰጠኝ ክስተት ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ በቦታው በነበረኝ ቆይታም አረመኔ፣ ጨካኞችና ለሰው ልጅ ይሉኝታ የሌላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች በሀገራችን እንዳሉ ተረድቻለሁ፡፡ ከራሳቸው ስሜት በስተቀር የሰው ቁስልና ስቃይ የማይሰማቸው ሰው መሳይ አውሬዎች እንዳሉ ታዝቤያለሁ፡፡ እግዚአብሔር በአምሳሉ ለፈጠረው የሰው ልጅ የማይጨነቁ የመንግሥት

አመራሮች በሀገራችን እንዳሉ በቆይታዬ ለመረዳት ችያለሁ:: የተፈናቀሉ ወገኖችን ቦታው ድረስ ሄደን በጠየቅንበት ወቅት የተፈናቃዮቹ ደስታና ያሳዩት የተስፋ ስሜት ለተመልካች ብዙ ያስተምራል:: ይኸውም በሀገራችን ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ ምክንያትና ፀጥታ ችግር ለተፈናቀሉና ለተጎሳቆሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች በቶሎ ልንደርስላቸው እንደሚገባ ያስተምረናል:: ሀብት አሰባስበን በየቦታው እየሄድን ተጎጂ ወገኖቻችንን በመጠየቅ ሐዋርያዊ ተልእኳችንን ባለመወጣታችን በበኩሌ ተሰምቶኛል:: ሁልጊዜም ቢሆን ከተገፉትና ከተጎሳቆሉት ጎን መቆም ያስፈልጋል:: በዚህ ዘመን ለአራዊት እንኳን ጥበቃ እየተደረገላቸው መብትና ክብራቸው በተከበረበት ወቅት በተቃራኒው ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ከአውሬ በታች ሁኖ እየታደነ የሚገደልበት ጊዜ ላይ መድረሳችን እጅግ ያሳዝናል::

ወገን በወገኑ ላይ ሰይፍ የሚያነሳበት ዘመን ላይ በመገኘታችን አብዝተን እንድንጸልይ እንድንጾም እንዲሁም የሆነብንን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲያስታግስልን ልንለምን ይገባናል:: ይህ መፈናቀልና ሞት እግዚአብሔር ጠብቆን ካልሆነ በስተቀር መላው ኢትዮጵያውያንን ደም የሚያቃባና ሀገራችንን ለከፋ ችግር የሚያጋልጥ እንስሳዊ ተግባር ነው:: እየተፈጸመ ያለው የአውሬያዊ ተግባር የሚፈጸመው በኢትዮጵያ ምድር መሆኑ አንዳንዴ ያጠራጥራል:: በውጭው ዓለም የምንሰማው የመጠፋፋት ተግባር በቅድስት ሀገራችን እየተከናወነ መታየቱ በእውነት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ራሱን ሊፈትሽና ለሰላም፣ ለፍቅርና ለአንድነት አጥብቀን እንድንሠራ የምንገደድበት ወቅት ላይ እንገኛለን::

የመፈቃቀር፣ የአንድነትና የሰላም ተምሳሌት የሆነች ሀገራችን በአንድ ጀንበር የሰው ልጆች መጠፋፊያ ምድር መሆኗ በጣም ያሳዝናል:: ሀገራችን ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆን አማኝ ያለባት ሀገር ናት ከተባለ ከእምነት አስተምህሮ ያፈነገጠ ድርጊት በሰው ዘር ላይ ሲፈጸም ምን እየሠራን ነበር? ‹‹ሰው ነን ሃይማኖትም አለን›› የሚሉ ሰዎች ከአውሬ ባላነሰ ሁኔታ በነፍስ ገዳይነት ሥራ ተሰማርተው ማየት በእውነት የከፋ ጊዜ እየመጣ መሆኑን ያመላክታል:: እነዚህ አካላት የሰው ህመምና ኀዘን የማይሰማቸው ጨካኝ ፍጥረቶች ናቸው:: እነዚህ መሰል ችግሮች እንዴትስ ነው? ዘላቂ መፍትሔ የሚያገኙት የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል:: የሃይማኖት አባቶች ትኩረት ሰጥተን ብንሠራ ኖሮ ለችግሮቻችን ሁሉ መፍትሔ ማምጣት እንችል ነበር የሚል እምነት አለኝ:: በትኩረት እየሠራን ባለመሆናችን ግን በሀገራችን ሰው መሠል አውሬዎች ተፈጥረው ሰውን የሚያሳድዱበትና የሚገድሉበት ጊዜ ላይ ደርሰናል::

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከሰማንያ በላይ አብያተ ክርስቲያናት ተዘግተዋል፤ በርካታ ካህናት ጽላት ይዘው ተሰደዋልና እርስዎ ይህንን ሲሰሙ ምን ተሰማዎት?

***ብፁዕ አቡነ አብርሃም፡-*** የተሰማኝ ስሜት መግለጫ የለውም፤ የምጠቀመው ቋንቋም ልቤ በኀዘን መሰበሩን ያስረዳኛል ብዬ አላምንም:: እንኳንስ የራስ የሆነች ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ሁና ማየት ይቅርና የሌላ ቤተ እምነትም ቢሆን እንደ ሃይማኖት አባትነቴ በጣም ያሳዝነኛል:: ጉዳዩ እጅግ ከማሳዘኑ የተነሳ በቦታው ተገኝቼ ባደረኩት ቅኝት በምእመናን በካህናት ላይ ከፍተኛ የሆነ ጭንቀትና መረበሽ አስተውያለሁ:: የተወሰኑ ካህናትም በአካባቢው ስለተጎዳችው ቤተ ክርስቲያን አናግረውኛል:: አንዳንድ አጥቢያዎች ላይ ጽላቶች እንዳልወጡም አጫውተውኛል:: በወቅቱም ከመተከል ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቶማስ ጋር መነጋገር እንዳለባቸው መክሬ ነገር ግን የባሕር ዳር ሀገረ ስብከትም አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ እንዲያደርግላቸው ተነጋግረናል:: ሊቀ ጳጳሱም ችግሩን ለመፍታት እየሠሩ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ:: ችግሮች በተደጋጋሚ በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ እየተከሰቱ ነው:: ስለሆነም ቤተ ክርስቲያንና እኛ አባቶች ልዩነትን አርቀን አንድነትን መስርተን የተጋረጠብንን ፈተና በጋራ በጥበብ ማለፍ ይጠበቅብናል::

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በበርካታ የሀገራችን ክፍሎች በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ እየተፈጸመ ያለው ጥቃት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዷል፤ ይህን በተመለከተ ቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ አለባት ይላሉ?

***ብፁዕ አቡነ አብርሃም፡-*** እኛ የሃይማኖት አባቶች ጠባቂ የበጎች እረኞች ተብለን ነው የተሰየምነው፡፡ እንደጠባቂነታችን ችግር የገጠማቸው ምእመናን ካሉበት ቦታ ድረስ በመሄድ ማጽናናትና መደገፍ ይጠበቅብናል፡፡ የምእመናን ኀዘን ኀዘናችን፣ ስቃያቸው ስቃያችን ፈተናቸው ፈተናችን ሊሆን ይገባል ነውም፡፡ ምእመናን ችግር ባጋጠማቸው ቁጥር በየሀገረ ስብከቱ ያሉ አባቶች ቦታው ድረስ ሄደው ምእመናንን መደገፍ፣ ማጽናናትና ከአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር በመመካከር ችግሩ በዘላቂነት የሚፈታበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ የምእመናን ስደታቸው ስደታችን ሞታቸው ደግሞ ሞታችን ሊሆን ይገባል፡፡

ምእመናንን በመጠበቁ ሂደት ላይ የሚመጣ የሕይወት መሥዋዕትነት ካለም ወደ ኋላ ማለት የለብንም፡፡ በጎችን በተኩላ አስነጥቆ የተማረከ ወታደር መስሎ መቀመጥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መሻር ነው፡፡ ይህንን ባናደርግ ደግሞ ከተጠያቂነት አናመልጥም፡፡ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ሲኖዶስ ደረጃ እውቅና ያለውና ዘመኑን የዋጀ ተወርዋሪና ጠንካራ ግብረ ኃይል ልታቋቁም ይገባታል፡፡ ይህ ግብረ ኃይል ችግሮች ከመፈጠራቸውና ከተፈጠሩ በኋላም የተበደሉትን የሚያስክስ፣ ፍትሕ የተጓደለባቸውን ፍትሕ የሚያሰጥ፣ የቤተ ክርስቲያንን ክብርና መብት የሚያስጠብቅ ይሆናል፡፡ ምእመናን በያሉበት ቦታ ሁሉ መብታቸውና ክብራቸው ተጠብቆ እንዲኖሩ የሚሟገትና የሚከራከር ይሆናል፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ይዞታዎች ያለ አግባብ ሲነጠቁ ወይም ለመንጠቅ አዝማሚያዎች ሲታዩ ቀድሞ ችግሩን የሚፈታ እንዲሆን ተደርጎ መዋቀር አለበት፡፡ ይህ ግብረ ኃይል ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ሰባክያነ ወንጌል፣ ካህናት አባቶችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁ በቀላል የምትታይ አይደለችም፡፡ እኛ ራሳችን እያቃለልናት፣ እያዳከምናትና እያሳነስናት ብንሆንም ጠላቶቿ ግን ግዙፋዊነቷንና ታላቅነቷን በማመናቸው ሁልጊዜም ቢሆን የጥፋት ኢላማ ያደርጓታል፡፡ ኢትዮጵያን ለማዳከምና ለመበታተን ቀድመው ቤተ ክርስቲያንን ያጠቃሉ፤ ያዳክማሉ፡፡ ጠላቶቻችን ሀገሪቱን እንዳልሆን ለማድረግ በቤተ ክርስቲያን ላይ ድሮም ሲያሴሩ ነበር፤ አሁንም እያሴሩ ይገኛሉ፡፡ የመተከሉ ፖለቲካ ቀውስ ሃይማኖታዊ ጭፍጨፋ ሀገርንም የማፍረስ ምልክት ነው፡፡ ይህ ተግባር የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የባዕዳን ድብቅ ሴራ ጭምር ነው፡፡ እርስ በርስ ማጫረስ፣ የፖለቲካ ተሳትፎ፣ የትጥቅ ልምድ የሌላቸውን ንጹሕ ለፍቶ አዳሪ ማጥቃትና ማስጠቃት የዛሬ ተግባር ብቻ ሳይሆን የቆየ ነው፡፡ ትላንት እንደዚህ ዓይነት አሳፋሪና አሳዛኝ ታሪክ ብናሳልፍም አሁን በዚህ ዘመን በንጹሐን ላይ እየተፈጸመ ያለው ግን እጅግ የተለየ ነው፡፡

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁ በቀላል የምትታይ አይደለችም፡፡ እኛ ራሳችን እያቃለልናት፣ እያዳከምናትና እያሳነስናት ብንሆንም ጠላቶቿ ግን ግዙፋዊነቷንና ታላቅነቷን በማመናቸው ሁልጊዜም ቢሆን የጥፋት ኢላማ ያደርጓታል፡፡**

# አባ ገላስዮስ

**በእህተ ሚካኤል**

የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ልጆች! እንደምን ከረማችሁ? አሜን የአባቶቻችን የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን!

ልጆች ትምህርታችሁን በንቃት እየተከታተላችሁ ነው? እያጠናችሁስ ነው? በርቱ ትምህርታችሁን በተገቢው መንገድ በመከታተል በመንፈሳዊም በሥጋዊም ዕውቀት ማደግ ይኖርባችኋል!

ልጆች! ዛሬ ይዘንላችሁ የቀረብነው አባ ገላስዮስ ስለሚባል ቅዱስ አባት ታሪክ ነው፤ መልካም ንባብ ይሁንላችሁ!

ልጆች አባ ገላስዮስ እግዚአብሔርን ከሚያመልኩና ከሚፈሩ ደጋግ ክርስቲያን ወላጆች የተገኘ ቅዱስ አባት ነው:: ቤተ ሰቦቹም ልጃቸው ገላስዮስን ከሕፃንነቱ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት እያስተማሩት በምግባርና በሃይማኖት ኮትኩተው አሳደጉት:: በኋላም ገላስዮስ የዲቁና ማዕረግ ተቀበለ::

ቅዱስ ገላስዮስም ከትንሽነቱ ጀምሮ ይህንን ዓለም በመናቅ ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር የሚተጋ መነኩሴ ሆነ:: በምንኩስና ሆኖ በጾም በጸሎት እየተጋደለ መኖር ጀመረ:: እግዚአብሔር አምላክም የቅዱስ ገላስዮስን ትጋት ተመልክቶ በአስቄጥስ ገዳም ባሉ መነኮሳት ላይ ቅስና ተሾመ:: በአስቄጥስ ገዳም ሆኖ በታላቅ ተጋድሎ የገዳሙን ማኅበረ መነኮሳት እያገለገለ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ ለአባ ጳኩሚስ እንደተገለጠ ለአባ ገላስዮስም ተገለጠለት::

በገዳሙ ያሉ መነኮሳትንም ሰብስቦ እግዚአብሔርን መፍራትንና የምንኩስናን ሕግ እንዲያስተምራቸው አዘዘው:: በገዳሙ የሚገኙ መነኮሳትን በመሰብሰብም መንፈሳዊ የሆነ የአንድነት ማኅበራዊ የኑሮን ሥርዓት ሠራላቸው:: አባ ገላስዮስም በመነኮሳቱ መካከል ሲኖር እጅግ ትሑት ከመሆኑ የተነሳ እንደ መምህራቸው ሳይሆን ከእነርሱ እንደሚያንስ እንደ አገልጋያቸው ይሆን ነበር::

አባ ገላስዮስ በአስቄጥስ ገዳም መነኮሳቱን በፍጹም የዋህነት፣ ቸርነትና በመታዘዝ ያገለግላቸው ነበር:: በዚያም ሳለ የብሉይ ኪዳን እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በአንድነት ሰብስቦ አንድ ታላቅ መጽሐፍ ጻፈ:: ይህን ታላቅ መጽሐፍ ለማጻፍም ፲፰ የወርቅ ዲናር አወጣ:: ያንንም ታላቅ መጽሐፍ መነኮሳቱ ለማንበብ በሚፈልጉ ጊዜ እንዲያገኙት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአትሮንስ ላይ አኖረላቸው::

አንድ ሰውም ከዕለታት በአንዱ ቀን አረጋዊ አባ ገላስዮስን ሊጎበኝ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጣ:: ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሲዘልቅም ማንም አልነበረም፤ ነገር ግን ያንን ታላቅ መጽሐፍ በአትሮንስ ላይ ተቀምጦ አየና ሊወስደው ፈለገ:: ጨለማ በሆነ ጊዜም ተመልሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጣና ማንም ሰው ሳያየው መጽሐፉን ሰርቆ ወጣ ሊሸጠውም ወደ ከተማ ይዞት ሄደ:: አንድ ሰውም መጽሐፉን ሊገዛው ፈልጎ ‹‹የመጽሐፉ ዋጋ ምን ያህል ነው? አለው::

ሌባውም ‹‹ ፲፯ የወርቅ ዲናር ስጠኝና ውሰደው›› አለው::

ገዢውም ‹‹ያልከውን ፲፯ የወርቅ ዲናር እሰጥሃለሁ ነገር ግን ለወዳጄ ወስጄ እስካሳየው ድረስ ጥቂት ታገሰኝ›› አለው:: ሌባውም በዚህ ስለተስማማ ገዢው መጽሐፉን ወደ አባ ገላስዮስ ዘንድ ይዞ በመሄድ ‹‹ አባቴ ሆይ! ይህ መጽሐፍ ተመልከትልኝ፤ መልካም ከሆነ እገዛዋለሁ›› አለው::

አባ ገላስዮስም መጽሐፉን ሊገዛ የመጣውን ሰው ‹‹ መጽሐፉን ሊሸጥልህ ያለው ሰው ምን ያህል ገንዘብ ጠየቀህ?›› አለው፡፡

ገዥውም ‹‹ ፲፮ የወርቅ ዲናር ጠየቀኝ›› በማለት ነገረው፡፡

አባ ገላስዮስም ‹‹መጽሐፉ መልካም ነው ዋጋው ቀላል ነው ግዛው›› አለው፡፡

ገዥውም ወደ ሌባው ተመልሶ እና አባ ገላስዮስ የነገረውን ደብቆ ‹‹ ለአባ ገላስዮስ አሳየሁት እርሱም ዋጋው በዝቷል አለኝ ›› አለው፡፡

ሌባውም ‹‹ያ ሽማግሌ ሌላ የተናገረህ ነገር የለም? ›› በማለት ገዢውን ጠየቀው፡፡

ገዢውም ‹‹አዎን ሌላ ምንም ነገር አልተናገረኝም›› አለው፡፡

በዚህ ጊዜ ያ መጻተኛ ሌባ ‹‹ ይህን መጽሐፍ በፍጹም አልሸጠውም›› ብሎ ወደ አባ ገላስዮስ ሄደ፡፡ ከእግሩ በታች ወድቆም ‹‹ ሰይጣን አስቶኛልና ይቅር በለኝ ፤ መጽሐፍህንም ውሰድ›› ብሎ ለመነው፡፡

የከበረ አባ ገላስዮስ ግን ‹‹ እኔ መጽሐፉን መውሰድ አልሻም ሽጠህ የወርቁን ዲናር ለምትፈልገው ተግባር አውለው›› አለው፡፡ ሌባውም በፊቱ እያለቀሰ እና እየሰገደ ብዙ ለመነው፤ ከብዙ ድካም በኋላ አባ ገላስዮስ መጽሐፉን ተቀበለው፡፡ ይህንንም ምሥጢር ከሁለቱ በስተቀር ማንም አያውቅም ነበር፡፡

ልጆች የአባ ገላስዮስን ደግነት አያችሁ? መጽሐፉን ሊገዛው የነበረው ሰው ይዞለት ሲመጣ ‹‹የኔ ነው፤ ተሰርቆ ነው›› ብሎ አላጋለጠውም ይህን ማድረጉ ሌባው የአባ ገላስዮስን መጽሐፍ በመስረቁ ተጸጽቶ እንደመለሰለት አስተውሉ፡፡

ልጆች! ከዚህ በኋላ ለአባ ገላስዮስ ትንቢት የመናገር ሀብት ተሰጠው፡፤ ብዙ ድንቅ ድንቅ የሆኑ ተአምራትን ያደርግ ነበር፡፡ በአንዲት ዕለትም የገዳሙ ወጥ ቤት የሚሠራው ሰው ለገዳሙ መነኮሳት ዓሳ ወጥ ሰርቶ አንዱን ልጅ በመጥራት ‹‹ እስክመለስ ድረስ ጠብቅ›› ብሎት ወደ ሥራው ሄደ፡፡ እንዲጠብቅ የታዘዘው ልጅ ግን ለገዳሙ መነኮሳት ከተቀመጠው ዓሳ በላ፡፡ ወጥ ቤት ሠራተኛውም ተመልሶ ሲመጣ ወጡ ተበልቶ በማግኘቱ ልጁን ‹‹ አረጋውያን አባቶች ሳይባርኩት እንዴት ደፍረህ ትበላለህ? አለው፡፡ የቁጣ መንፈስም በልቡ አደረና ልጁን ረግጦ ገደለው፤ ልጁ ፈጽሞ እንደሞተ አይቶ እጅግ ደነገጠ፡፡

ታላቅ ፍርሃትም ፈራና ወደ አባ ገላስዮስ ሄዶ የሆነውን ሁሉ ነገረው፡፡ አባ ገላስዮስም ወጥ ቤት ሠራተኛውን ‹‹የልጁን ሬሣ ወስደህ ከቤተ መቅደሱ ፊት አስተኛው›› በማለት አዘዘው፡፡ ወጥ ቤት ሠራተኛውም አባ ገላስዮስ እንዳዘዘው አደረገ፡፡ ማታም በሆነ ጊዜ አረጋውያን መነኰሳት በቤተ ክርስቲያን ጸሎት አድርገው ወጡ፡፡ አረጋዊ አባ ገላስዮስም ከእነርሱ ጋር በወጣ ጊዜ የሞተው ልጅ ተነሥቶ ከኋላው ተከተለው ይህንን ማንም አላወቀም ነበር፡፡

እርሱም የገደለውን ባለወጥ ለማንም እንዳይናገር አዘዘው፡፡ የተመሰገነ አባ ገላስዮስም ያማረ ትሩፋቱንና ተጋድሎውን ፈጽሞ ፤ እግዚአብሔርን አገልግሎ ፤ይህንንም በጎ ተግባር መታሰቢያ ትቶ ከዚህ ከኃላፊው ዓለም በሰላም ዐረፈ፡፡

ልጆች ከታሪኩ ብዙ መንፈሳዊ እውቀት እንደቀሰማችሁ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በሚቀጥለው ትምህርታችን እስክንገናኝ በትምህርታችሁ ጎብዛችሁ እንድታጠኑ ደግሞም በጸሎትና በጾም እንድትበረቱ እንመክራችኋለን፤ ደኅና ሰንብቱ!

*ልጆች! የአባ ገላስዮስ ረድኤት በረከቱ ይደርብን በጸሎቱ ይማረን አሜን!*

*ምንጭ ፦ ስንክሳር የካቲት ፲፪*

# «ምን አለበት»

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

ክርስትና ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ይጠራል፤ የጠራቸውን ደግሞ አስተምሮ አጥምቆ ይመርጣል፤ የመረጣቸውን ደግሞ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አሳድጎ ያጸድቃል።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን የአንድ ክርስቲያን ጉዞው ቤተ ክርስቲያን በሠራችው ሥርዓት ውስጥ ነው። ያለሥርዓት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስጠትም ይሁን መቀበል አይቻልም። በመሆኑም ያለሥርዓት መመላለስ ለቤተ ክርስቲያን አለመታዘዝ ነው። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የክርስቶስ አካል ስለሆነች ለክርስቶስ አለመታዘዝ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን።›› ፩ኛ ቆሮ ፲፬÷፵ ይላል።

ለአንዳንዶች ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አላስፈላጊ፣ ተደራቢ፣ ትርፍ ነገር ይመስላቸዋል። ለኦርቶዶክሳውያን ግን አግባብ በሆነ መንገድ እግዚአብሔርን ለማምለክ አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል። በመሆኑም ቅዳሴው፣ ጥምቀቱ፣ በዓላቱ፣ ጾሙ፣ ትምህርቱ /ስብከቱ/ ወዘተ በሥርዓት የሚከናወን ነው።

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንደ አካባቢው ሁኔታ፣ እንደ ማኅበረሰቡ አኗኗርና ልማድ ከኃጢአት ወይም ለኃጢአት ከሚያበረታታ ሁኔታ በጸዳ፣ ቀንበር ሆኖ ለምእመናንም ሆነ ካህናት የማያደናቅፍ ሆኖ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርጎ፣ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ተዘጋጅቶ በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ መመሪያ የሚሆን ነው።

ይህንን ባለመረዳት አንዳንድ ምእመናን በቤተ ክርስቲያናችን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ውስጥ መከበር ያለባቸውን ሥርዓቶች ‹‹ምን አለበት›› በሚል መንፈስ ሲጥሷቸው፣ ለሌሎችም የስንፍና ምሳሌ እየሆኑ ይታያሉ። ለምሳሌም በቤተ ክርስቲያ ቅዳሴ ሲደረግ መከበር ያለባቸው ሥርዓቶች ከአለማወቅ እስከ መናቅ ችግሮች ይታያሉ። ለዚህም የተወሰኑትን ማስታወስ እንችላላን።

የመጀመሪያው ችግር ሥርዓተ ቅዳሴ በሚፈጸምበት ጊዜ መግቢያ መውጫ ሰዓቶችን አለማክበር ነው። የሥርዓተ ቅዳሴ መግቢያ መውጫ ማወቅ በሥርዓቱ በአግባቡ ለመሳተፍ የሚከናወንበትን ጊዜ ማወቅ ያስፈልጋል። መቼ ቀን በምን ሰዓት ይገባል፤ ይወጣል የሚለውን ማወቅ ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን ራስን በሥርዓቱ በተገቢው ጊዜ ጀምሮ በተገቢው ጊዜ በመፈጸም እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ ለመሳተፍ ያስችላል። ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ ሌሎች በሚገባው ጊዜ ገብተው በቅዳሴው የሚሳተፉ ትጉሃንን ያለጊዜው በሚገቡና በሚወጡ ሰዎች ሳይታወኩ አገልግሎቱን እንዲሳተፉ ያደርጋል። በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ አባቶቻችን ለሠሩት ሥርዓት በመታዘዝ ፍቅራችንን እንገልጻለን። ሌላውና ዋነኛው ነገር ደግሞ የእግዚአብሔር ስሙ በትጉሃን በተመስጦ በሚጠራበት በሚወደስበት የአምልኮት ሰዓት እንደ ሥርዓቱ በመመላለስ አምላካችንን እናከብራለን።

ሌላው አለባበሳቸውን እንደሥርዓቱ ማድረግ ሲገባቸው ያለሥርዓት ለብሰው በቅዳሴው የሚሳተፉ ሰዎች ምን አለበት የሚል አቋም ሲያራምዱ ይታያሉ። በቅዳሴ ሥርዓት ጊዜ አካልን የሚያራቁቱ፣ የተለያዩ ትኩረት የሚስቡ ዓላማዊ መልእክት የተጻፈባቸው ልብሶችን፣ ለስግደት ለእንቅስቃሴ የማይመቹ ወዘተ ልበሶችን መልበስ አግባብ አይሆንም። ሴቶች ራሳቸውን ሸፍነው፣ እንደሴትነታቸው ለብሰው፣ ወንዶችም እንደወንድነታቸው ለብሰው በተቻለ መጠን ሁላችንም ብርሃናዊ በሆነ

አገልግሎት እየተሳተፍን መሆኑን በሚገልጽ መንገድ ነጭ ነጠላ /ለብስ/ መስቀልኛ አጣፍተን መሳተፍ አለብን፡፡ ሴቶችም ወንዶችም በቅዳሴ ለመሳተፍ ሲመጡ ለሥርዓቱ በሚገባ ከማኅበረ ምእመናን አንድ ሆነን በምንታይበት፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በምናሳይበት መንገድ መልበስ ያስፈልጋል፡፡

ለቅዳሴ መጥተው የራሳቸውን የጸሎት መጽሐፍ አንብበው የሚመለሱ ሰዎችም ያጋጥማሉ፡፡ በቅዳሴው ጸሎት በንቃት እንዲሳተፉ በግል ከምንጸልየው ጸሎት በላይ በኅብረት በፍቅር የምንሳተፍበት የቅዳሴ ጸሎት እንደሚበልጥ ሲነገራቸው ‹‹ምን አለበት›› የሚሉ ወገኖችም አሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች የቅዳሴውን ጣዕምና መልእክት ካለመረዳት፣ በውስጡም ያለውን የምስጢርና አገልግሎት ታላቅነት ካለመረዳት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ጉዳይ ‹‹ለምን?›› ብሎ ከመጠየቅ ይልቅ ‹‹ምን አለበት!›› የሚለውን አስተሳሰብ መከተል ሥርዓት አምልኮን አለመረዳትና መናቅ ነው፡፡

የቅዳሴ ጸሎት ከሁሉ ጸሎት የሚበልጥ የወንጌል መልእክት ያለው፣ ምክር፣ ተግሳጽና ትምህርት የያዘ ነው፡፡ ከትንሽ እስከ ትልቅ ከአካባቢ እስከ ዓለም ላለው ሕዝብና ተፈጥሮ ሁሉ የምጸልይበት ነው፡፡ የምንወደውን እግዚአብሔርን በታላቅ ትሕትና ስሙን እየጠራን የምናከብርብት፣ የምናመልክበት ጸሎትና ምስጋና ያለው ነው፡፡ ከሁሉም በላይ የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውና ደሙ የሚፈተትበት ንስሐ ለገቡ ምእመናን የሚሰጥበት ታላቅ ጸሎት ነው፡፡ ስለዚህ የራሳችን የግል ጸሎት በምናደርስበት ጊዜ በቤትም ይሁን በቤተ ክርስቲያን በሚገባው የግል የጸሎት ሥርት መደረግ ያለበት ነው፡፡

ሌላው ዘመን አመጣሹ ፈተና ደግሞ የሞባይል ስልኮች አጠቃቀም ነው፡፡ በቅዳሴ ጊዜ ስልኮቻቸውን የማያጠፉ፣ ወይም ድምፀ አልባ የማያደርጉ ከዚያም አልፈው የፌስ ቡክና የቴሌግራም ገጾችን ከፍተው የሚጠቀሙ፣ መልእክት የሚለዋወጡ፣ ወዘተ ሰዎች አሉ፡፡ እንዲህ ያሉት ወገኖች ሲመከሩ አንዳንዶቹ ‹‹ምን አለበት፤ ከዘመኑ ጋር መራመድ ነው›› ብለው የሚያስቡ አሉ፡፡

ይህ ግን በቅዳሴ ጊዜ ያለንን ተመስጦ የሚሰልብ፣ ‹‹እናስተውል›› ከሚለው የሥርዓተ ቅዳሴ ትእዛዝ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ የቅዳሴ ጊዜ ለእግዚአብሔር ብለን ለይተን የሰጠነው ጊዜ ከሆነ በዚያን ጊዜ ከእርሱ የሚበልጥ የምናከብረውና የምናተኩርብት ነገር ሊኖር አይገባም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ አንዳንድ ምእመናን በአለማወቅ የሚፈጽሟቸው የሥርዓት ጥሰቶች አሉ፡፡ እንዲህ ያሉትን ምእመናን በልዩ ልዩ መንገድ ሥርዓትን እንዲያውቁ ማስተማር አግባብ ነው፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ በዚያው ሥርዓተ ቅዳሴ በሚፈጸምበት ዕለት ከሚሰጡ ትምህርቶች ጋር አጣምሮ መምከር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ እጅግ አስቸጋሪው ግን ነገሩን በአለማወቅ ብቻ ሳይሆን እንዲያውቁት ሲነገራቸው ‹‹ምን አለበት!›› ለሚሉ ወገኖች በተደጋጋሚ ምክርና ትምህርት መስጠት የሁሉም ምእመናንና አገልጋዮች ድርሻ ነው እንላለን፡፡

# ንሰሐ አባቴን የደበቅሁት ምሥጢር፡- ወደ ኋላ መመለስ ፈራሁ

**ክፍል አንድ**

ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች እንደምን ሰነበታችሁ? ለረጅም ጊዜ በውስጤ ሲመላለስ የቆየ እና ሰላም የነሳኝን ጥያቄ ልጠይቅ ወደድኩ የኅሊና ዕረፍት የሚሰጥ መልስ ትሰጡኛላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ስሜ ወለተ ገብርኤል ይባላል ዕድሜዬ በአርባዎቹ አጋማሽ ላይ የሚገኝ ሲሆን ባለ ትዳርና የሦስት ልጆች እናት ነኝ፡፡ ትዳር ከመመሥረቴ በፊት ከተለያዩ ወንዶች ጋር ተራክቦ እፈጽም ነበር፡፡ የአሁኑን የትዳር አጋሬን ሳገባ ይህንን አልነገርኩትም ነበር፡፡ በጊዜው ከሱ በፊት ከነበረኝ የወንድ ጓደኛዬ ጋር በአጋጣሚ በተፈጠረ ክሥተት ስህተት ላይ መውደቄን ብቻ ነግሬው ነው ያለፍኩት፡፡ ለንስሐ አባቴም በወቅቱ ያለፈ ሕይወቴን እና የሠሁትን ኃጢአት በሙሉ ዘርዝሬ አልነገርኳቸውም፡፡ ለአሁኑ ባለቤቴ የነገርኩትን ብቻ ነግሬ ሌሎቹን ‹‹ያለፈ ታሪክ ነው›› በሚል ምክንያት ሸፋፍኜ ነው ያለፍኩት፡፡ በዕድሜ እየበሰልኩ ስመጣ እና ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው ውስጤ ይደነግጣል፤ በኅሊናዬም ኃጢአተኛ እንደሆንኩ እያስታወሰኝ በየዕለቱ ይወቅሰኛል፡፡ ከዚህም የተነሣ መልካም ለሆነው ባለቤቴ፣ ለልጆቼ፣ ለንስሐ አባቴ በተለይም ለእግዚአብሔር ታማኝ እንዳልሆንኩ ይሰማኛል፡፡

ውድ የስምዐ ጽድቅ አዘጋጆች! ያለፈውን ኃጢአቴን እያሰብኩ በየዕለቱ ፀፀት ቢሰማኝም በጊዜው የደበቅሁትን ምሥጢር ግን አውጥቼ መናገር ፈራሁ፡፡ ለመሆኑ ያለፈ በደሌን ዛሬ ላይ አለመናዘዜ ኃጢአት ይሆን? ፀፀቴን መሸከም ባለመቻሌ ለባለቤቴ እና ለንስሐ አባቴ መንገር እፈልግና ወደ ኋላ መመለስ ፈራሁ፡፡ ምን ላድርግ ምንስ ትመክሩኛላችሁ እባካችሁ ዘርዝር አድርጋችሁ አስረዱኝ፡፡

እህታችን ወለተ ገብርኤል ‹‹የንስሐ አባቴን የደበቅሁት ምሥጢር ኅሊናዬን ዕረፍት ነሳኝ ወደ ኋላ ተመልሼ መናዘዝን ፈራሁ ምን ይሻለኛል?›› በማለት መፍትሔ ለማግኘት ጥያቄ ፤ማቅረብሽ መልካም ነው እንላለን፡፡ ምክንያቱም ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት “ምክር ሠናይት ለኵሉ ዘይገብራ፤ ለሚያደርጋት ሁሉ ምክር መልካም ናት” (መዝ.፻፲፣፲) በማለት እንደተናገረው ሰው በሥጋው ሲታመም ለመታከም ታክሞም ለመዳን የሚሄደው ወደ ጤና ተቋም እንደሆነ ሁሉ ነፍስም በኃጢአት ደዌ ስትያዝ (ስቴታም) መድኃኒቷ የእግዚአብሔር ቃል ፤ወደ እርሱም በንስሐ መቅረብና በውስጥሽ ረፍት ለነሳሽ የነፍስሽ ሕመም መፍትሔ አገኛለሁ ብለሽ ይህንን ጥያቄ ይዘሽ ወደ ዝግጅት ክፍላችን ቀርበሻል፡፡ ስለሆነም እኛም እንደተለመደው የመምህራን አባቶችንና የቅዱሳት መጻሕፍትን ሐሳብ አብነት አድርገን ለችግርሽ መፍትሔ ይሆናሉ ያልናቸውን ምክረ ሐሳቦች ከዚህ በታች እንደሚከተለው አቅርበናልና በጥሞና እንድትከታተዪን በእግዚአብሔር ስም እናሳስብሻለን፡፡

ውድ እኅታችን ዕድሜሽ በዐርባዎቹ አጋማሽ ላይ እንደሆነ እና በትዳር ተወስነሽ የሦስት ልጆች እናት እንደሆንሽ ገልጸሽልናል፡፡ ኅሊናሽን ዕረፍት የነሣሽ ጉዳይም ከአሁኑ የትዳር አጋርሽ ጋር ከመጣመርሽ በፊት ከተለያዩ ወንዶች ጋር ተራክቦ መፈጸምሽን ይህንን ጉዳይ ለነፍስ አባትሽም ሆነ ለትዳር አጋርሽ በግልጽ (በዝርዝር) እንዳላስረዳሻቸው ይህም አሁን ላይ ለነፍስ አባትሽ አለመናገርሽ እየረበሸሽ እንደሆነ ገልጸሽልናል፡፡

እኅታችን ወለተ ገብርኤል ላነሳሽው ጥያቄ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልስ ሊሆን የሚችለውን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

ሰው አስቀድሞ ሲፈጠር ለባዊት፣ ነባቢት እና ሕያዊት ነፍስ ተሰጥቶት አዋቂ አእምሮ ታድሎት የተፈጠረ ታላቅና ድንቅ ፍጡር ነው፡፡ ስለዚህ አስቀድሞ ማወቅ የሚገባቸው ነገሮች አሉ፡፡ እንደማንኛውም ላለፈውም ሆነ ይልቁንም

አሁንም መረዳት የሚኖርብሽ ነገሮች የምንላቸውን እንደሚከተለው እንዘርዝራቸዋለን፡፡

**ሀ. የሰይጣንን ሴራ መረዳት፡-** ሰይጣን በሰው ልጅ ከመቅናት መቼም አያርፍም፡፡ በመጽሐፈ ቀለሚንጦስ “ወሶበ ርእየ ሰይጣን ሀብተ ጸጋ ለአዳም እምኀበ እግዚአብሔር ቀንዓ ላዕሌሁ እይእቲ ሰዓት፤ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ለአዳም የተሰጠውን ጸጋ ባየ ጊዜ ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ቀና” (ቀለ.፩፣፵፮) ተብሎ ተጽፎ እንደምናገኘው የሰውን ልጅ በሕይወት መኖር የማይወድ ጥንተ ጠላት ዛሬም ያለማቋረጥ ይከታተለዋል፡፡ በመሆኑም መጀመሪያ ኃጢአት እንዲሠራ መገፋፋት ከሠራው በኋላ ደግሞ ራሱን ለንስሓ እንዳያዘጋጅ በመከልከል ግን በሠራው ኃጢአት ከአቅም በላይ እንዲጨነቅ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ዘላቂ የሆነ መፍትሔ ለማግኘት እንዲህ ያለውን የሰይጣንን ክፉ ሴራ በአግባቡ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

**ለ.የንስሓን ምንነትና አስፈላጊነት በአግባቡ መረዳት፡-** ንስሓ መጸጸት መመለስ ፊት በሠሩት መጥፎ ሥራ ማልቀስ ፊት የሠሩትን ሥራ ላለመሥራት መወሰን ማለት ነው፡፡ ንስሐ የተሰበረ መንፈስ ነው፡፡ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ‹‹መሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር መንፈስ የዋሕ ልበ ትሑተ ወየዋሐ ኢይሜንን እግዚአብሔር፤ የእግዚአብሐር መስዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው የተሰበረውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም፡፡›› (መዝ. ፶፥፲፯) በማለት እንደገለጸው ሰው የተሰበረ ልብ ሲኖረውና የቀና መንፈስ ሲላበስ ያኔ ነው የንስሓ ሰው ሆነ የሚባል፡፡ የንስሓ ጀማሪ የሰው ልጆች ሁሉ አባት የሆነው አዳም ነው ፡፡ አትብላ የተባለውን ዕፀ በለስ በበላና ከክብር በተዋረደ ጊዜ እጅግ አብዝቶ አነባ እንባው አልቆ እዥ እስከሚወጣው ድረስ አለቀሰ፡፡ ኃጢአትን መናዘዝ የተጀመረውም በብሉይ ኪዳን ይልቁንም በሕገ ልቡና ነው፡

**ንስሓ ከእግዚአብሔር የምንታረቅበት፡-** አባቱ ‹‹ይህ ልጄ ሞቶ ነበር አሁን ግን ሕያው ሆኗልና ጠፍቶም ነበር ተገኝቷልና፡፡ ›› (ሉቃ. ፲፭፥፳፬) ፤ ከሞት የምንድንበት ሉቃ.፲፫፣፩-፭፣ ሁለተኛ የምንወለድበት ነው ሊቁ ቅዱስ አትናቴዎስ በቅዳሴው ሦስት ልደታት ብሎ ከሚዘረዝራቸው መካከል አንዱ ንስሓ ነው፡፡ “ንሕነኒ እለ ተወለድነ በሥጋ ከማሆሙ ብነ ሠለስቱ ልደታት፡፡ አሐቲ ጥምቀት ቀደስት እንተ ትሬስየነ አምሳለ ክርስቶስ፡፡ ወአሐዱ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ ዘይሠሪ አበሳ ወኃጢአተ፡፡ ወአሐዱ አንብዕ ዘበንስሓ ዘይወጽእ እምውስጥ በአምሳለ ዮርዳኖስ ዘያቀርብ ንጹሐ ቅድመ እግዚአብሔር፤ እኛም እንደነሱ በሥጋ የተወለድን ሦስት ልደታት አሉን፡፡ አንዷቱ የክርስቶስ ምሳሌ የምታደርገን ቅድስት ጥምቀት ናት፡፡ ሁለተኛው ኃጢአትንና አበሳን የሚደመስስ የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ ነው፡፡ ሦስተኛው በዮርዳኖስ አምሳል ከውስጣችን የሚወጣው በንስሓ የሚገኝ ዕንባ ነው፤ ይህም በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ አድርጎ የሚያቀርብ ነው” (ቅዳሴ አትናቴዎስ እንዲል፡፡ ንስሓ እንደ አባቶቻችን አስተምህሮ የበደለውን እንዳልበደለ፣ ዘማዊውን እንድ ድንግል፣ ኃጢአተኛውን እንደ ጻድቅ የምታድርግ ናት፡፡

**ሐ. ከንስሓ አባት ምንም ሊደበቅ የሚችል ነገር እንደሌለ መገንዘብ፡-** የንስሓን አስፈላጊነት በተመለከተ ከላይ የተዘረዘሩትን ከላይ በሚገባ የተረዳ ሰው ንስሓ ለመግባት ወደኋላ አይልም፡፡ ከንስሓ አባቱ ፊት ቀርቦም ይህን ልናገር ይህን ደግሞ አልናገር ብሎ የሚመርጠውና የሚያስቀረው አንዳች ነገር ሊኖረው አይችልም፡፡

እግዚአብሔር መሐሪ ስለሆነ ዕድሜ ለንስሓ እየሰጠን እንጂ የንስሓ አባትን መዋሸት እግዚአብሔርን መዋሸት ስለሆነ ያስቀጣል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካቸው ተጽፎ የምናገኘው ሐናንያና ሰጲራ ቅዱስ ጴጥሮስን ባታለሉት ጊዜ ተቀጥተዋል፡፡ (ሐዋ. ፭፣፩-፲፩) ከካህኑ መደበቅ ከመንፈስ ቅዱስ መደበቅ ማለት ነው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም ሐናንያን ሲወቅሰው “ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ታታልል ዘንድ የመሬቷንም ዋጋ ከፍለህ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ እንዴት አደረ?” (ሐዋ. ፭፣፫) በማለት የተናገረው ካህኑን ማታለል መንፈስ ቅዱስን ማታለል ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ዛሬም ምን አልባት አረፈድሽ እንጂ

እንዳልመሸብሽ ማወቅና ፈጥነሽ ወደ ንስሓ አባትሽ መሄድ ዋነኛ መፍትሔው መሆኑን ነው።

**መ. በንስሓ ሕይወት የተጠቀሙ ሰዎችን ማሰብ፡-** ንስሓ እግዚአብሔር አምላካችን የሰውን ልጅ በምን ያህል መጠን እንደሚወደው የገለጸበት ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር ንስሓቸውን ተቀብሎላቸው ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ የታደጋቸው በርካታ አባቶችን መዘርዝር ይቻላል። ይሁን እንጂ ለዚህ ጉዳይ ብቻ የተወሰኑትን እንጥቀስ።

## ፩. አዳም

ንስሓ በመግባታቸው ከእግዚአብሔር ጋር የታረቁ ብዙ ቅዱሳንን ማንሣት ይቻላል። ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ ከዘመነ አበው አባታችን አዳም ከእግዚአብሔር ተጣልቶ ከልጅነት ወጥቶ ከገነት ተባሮ የነበረው በድሎ ሳለ ተክሦለት ወደቀደመ ክብሩ ልጅነት ወደቀደመ ቦታው ወደ ገነት የተመለሰው በንስሓ ነው። ‹‹ወኮነ አራቂ ለሐዲስ ኪዳን፤ ለሐዲስ ኪዳን አስታራቂ ሆነን። ›› በማለት ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም እንደገለጸው አስታራቂው ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ ከአብ፣ ከራሱና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በደሙ ፈሳሽነት ያስታረቀን ሲሆን ለዚህ እንድንበቃ ምክንያት የሆነን አዳም የገባው ንስሓ ነበር።

## ፪. ነቢዩ ዳዊት

በዘመነ ነቢያት በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ከተመለሱ ታላላቅ አባቶች መካከል ነቢዩ ዳዊትን መጥቀስ ይቻላል። ዳዊት የጎልማሳ ሚስት ቀምቶ ጎልማሳ አስገድሎ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ ነበር። እግዚአብሔርም እጅግ ተቀይሞት ነበር። በነቢዩ በናታን አማካኝነትም እንዲህ ሲል ወቀሰው። “በእስራኤል ላይ ንጉሥ ልትሆን ቀባሁህ፤ ከሳኦልም እጅ አዳንሁህ፤ የጌታህንም ቤት ሰጠሁህ፤ የጌታህንም ሚስቶች በብብትህ ጣልሁልህ፤ የእስራኤልንና የይሁዳን ቤት ሰጠሁህ፤ ይህም አንሶህ ቢሆን ኖሮ ከዚህ የበለጠ እጨምርልህ ነበር። አሁንስ በፊቱ ክፉ ትሠራ ዘንድ የእግዚአብሔርን ነገር ለምን አቃለልክ ኬጢያዊውን ኦርዮን በሰይፍ መተሃል፤ ሚስቱንም ለአንተ ሚስት ትሆን ዘንድ ወስደሃል፤ እርሱንም በአሞን ልጆች ሰይፍ ገድለሃል።” (፪ሳሙ. ፲፪፥፯-፲) እንዲል።

ከላይ ባነበብነው አንቀጽ ነቢዩ ዳዊት በእግዚአብሔር ዘንድ ተወቀሰ። ዳዊትም ወቀሳው ሲመጣበት እንዲሁ ዛሬ ነገ እያለ ጊዜ አላባከነም። ምሕረት የባሕርዩ የሆነ አምላክ የውስጡን እንደሚያውቅና ምሕረትን እንደሚያደርግለት በማመን በፍጥነት ንስሐ ገባ። የዳዊት ንስሓ በዕንባ የተሞላ እውነተኛ ጸጸት ያለበት እንደነበር አበው ያስረዳሉ። እርሱም በመዝሙሩ ‹‹ወአሐጽብ ኵሎ ሌሊተ አራትየ ወበአንብዕየ አርሐስኩ ምስካብየ፤ ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ በዕንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ›› (መዝ. ፮፥፮) በማለት ተናገረ። ምሕረት የባሕርዩ የሆነው እግዚአብሔርም ታረቀው። ለእኛ የሚያስፈልገንን ሁሉ እኛ ሳንለምነው ያዘጋጅልናል። የተሰጠንን ጸጋ ባለመረዳትና በደካማ ባሕርያችን እንኳን ብንበድለው ስንመለስ ንስሓችንን ለመቀበል ቸር አባት ነው።

**የንስሓ ጀማሪ የሰው ልጆች ሁሉ አባት የሆነው አዳም ነው ። አትብላ የተባለውን ዕፀ በለስ በበላና ከክብር በተዋረደ ጊዜ እጅግ አብዝቶ አነባ እንባው አልቆ እዥ እስከሚወጣው ድረስ አለቀሰ። ኃጢአትን መናዘዝ የተጀመረውም በብሉይ ኪዳን ይልቁንም በሕገ ልቡና ነው፡**